# መፍጠንና መፍጠር

## የወል እውነቶችን የማጽናት ቀጣይ የትግል ምእራፍ

# ይዘት

1. መግቢያ
2. ተለዋዋጭ አለም፤ ሥር የሰደዱ ሀገራዊ ችግሮች
3. የፈጠራና ፍጥነት አስፈላጊነት
4. የመፍጠን ጅማሮ ስኬቶች፣
5. ከፍጥነት የሚገቱን፣
6. ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን፣
7. ማጠቃለያ፣

# መግቢያ

- የብልጽግና ቀዳሚ አጀንዳዎች

ስርዓት መገንባት፣

የሕዝብን ህይወት መለወጥ፣

# ለዘመናት ሲወሳሰቡ የቆዩ ችግሮች



ድህነት


አክራሪነት እና ጽንፈኝነት

የሀገረ መንግስት ግንባታ እንከኖች

ያለንበት ቀጠና ጂኦፖለቲካዊ ተጽዕኖ

# የቀጣይ አመታትን የአለም የሀይል አሰላለፍ የሚወስኑ አዝማሚያዎች

የብዝሃ ሀይል አሰላለፍ መፈጠር



የመንግስት ሀይልና ስልጣን መዳከም

የድህረ እውነታ ፖለቲካ መስፋፋት

# የእስካሁን ዋና ዋና ስኬቶቻችን

1. ከፍተኛ ምርታማነት፣
2. የተቋማት ግንባታ፣
3. ህልውናን ያስቀጠለ ድል፣

# ያጋጠሙን ዋና ዋና ፈተናዎች

01 የዋጋ ንረት ችግር፣


02 የሰላም እጦት እና ያለመረጋጋት፣

03 የስራ አጥነት ችግር፣

04 ተለዋዋጭ የዓለም ሁኔታ፣



# የለውጥ ስኬቶቻችን መመዘኛዎች



# የለውጥ ምዕራፎች

# የመጀመሪያ ምዕራፍ
# የመጀመሪያ 2 አመት

- ብዙ ሙቀትና መደበላለቅ የነበረበት፣

መርህ እና መርህ አልባነት



ዲሲፕሊን እና ዲሲፕሊን አልባነት

ደጋፊነት እና ተቃዋሚነት

# ሁለተኛ ምዕራፍ
# በመደመር መንገድ መጓዝ የጀመርንበት 3 አመት

መለስ ቀለስና ወደኋላ ጎታቾች የበዙባት ሀገር

ወደራስ መሳብና መጥለፍ የነበረበት



ብርቱ ጦርነት የተከፈተበት

ያልጠሩ ነገሮች የበዙበት

# የማጥሪያ ምዕራፍ

የተጣለውን መሰረት በመጠቀም የለውጥ ጉዞውን ፍጥነትና ቀጣይነት የምናጠናክርበት

አመራርና አባል የማጥራት እና የማብቃት ሥራ የምንሰራበት

# ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች፣

01. ፈጠራ እና ፍጥነትን በማከል በትጋት መስራት

02. ሀገራዊ አንድነታችንን በህብረ ብሔራዊ መሰረት ላይ መገንባት

03. የሁሉም ህዝቦች የወል እውነቶች እና ሐሳብ ማዕከላዊ ስርዓቷ የሆነች ኢትዮጵያን በጽኑ መሰረት ላይ መገንባት

04. ድሎችን ማስቀጠል፣ በአፈፃፀም በደከምንባቸው ተግባራት ላይ ፈጠራ እና ፍጥነታችንን በመጨመር ህብረ ብሔራዊነትን ማጽናት

05. የአመለካከት ጥራትና የአሰላለፍ ግልጽነት መፍጠር እና አደረጃጀቶች በሙሉ አቅማቸው ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ

# ክፍል አንድ

# ተለዋዋጭ አለም፤ ሥር የሰደዱ ሀገራዊ ችግሮች

# 1. ተለዋዋጭ ዓለም፣ ስር የሰደዱ ሀገራዊ ችግሮች

1.1 ከባለአንድ ዋልታ ወደ ብዝኃ ዋልታ እየተቀየረ ያለ የዓለም የኃይል አሰላለፍ፣

- የምስራቅ ሀገራት በኢኮኖሚና በወታደራዊ አቅም ማደግና ስትራተጂያዊ ትስስር መፍጠር፣
  - ⇨ቻይና፣ ሩሲያ፣ ቱርክ፣ ኢራን፣ ሕንድ እና ሌሎች የBRICS ሀገራት፣
  - ⇨በቅርቡ በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የታዩ ለውጦች፣

# 1.1 ከባለአንድ ዋልታ ወደ ብዝኃ ዋልታ .....

- አሜሪካ የዓለም አቀፍ ግንኙነት መርኋን ከፀረ ሽብር ትብብር ወደ ጂኦፖለቲካና ወደ ኢኮኖሚ ግንኙነት እየቀየረች ነው፣
- የዩክሬን ሩሲያ ጦርነት የጎራ አሰላለፉን አፋጥኖታል፣
- በምስራቅ ጎራ የተጀመረው የዶላር እቀባ፣
- አፍሪካ በተለይም የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የብዙ ኃይላት መፎካከሪያና መፋለሚያ ሜዳ ሆኗል።
  - ✓ቀይ ባህርና ጂኦፖለቲካዊ ተጽእኖ፣


# 1.1 ከባለአንድ ዋልታ ወደ ብዝኃ ዋልታ .....

- በፀጥታ ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ የማግኘት ጥያቄ፣
- የኢትዮጵያ ከኃያላን መካከል ለአንዱ ሳያጋድሉ ሚዛንን ጠብቆ የመጓዝ አቅጣጫ፣
- የውስጥ አንድነትና አስተማማኝ ሰላም ወሳኝነት፣
- ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቀንድ ምልክት ናት፣
  - ✓የቆዳ ስፋት፣ የሕዝብ ብዛት፣ ታሪክ፣ ኢኮኖሚ እድገት፣ የሰላም ማስከበር ሚና፣ የተፈጥሮ ሀብቶች መገኛ፣ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ፣ በድንበርና በውኃ ከ13 አፍሪካ ሀገራት ጋር የምትገናኝ፣ በጂኦፖለቲካ ተፈላጊ በሆነ ቦታ ላይ መገኘታችን እድልም ስጋትም መሆኑ፣

# 1.1 ከባለአንድ ዋልታ ወደ ብዝኃ ዋልታ .....

በግጭትና በእርስ በርስ ጦርነት የሚታመሱ ሀገራት የሚበዙበት

ደካማና ዘላቂ ጥቅማቸውን ማስከበር የማይችሉ ሀገራት ያሉበት




በሀገራት ውስጣዊ ፖለቲካ እጅን ሰድዶ የሚፈተፍት የሚበዛበት

በውስብስብ ሽኩቻ እና ተለዋዋጭ በሆነ ስጋት የተከበበ ነው

# እንደ ኢትዮጵያ



01 ውስጣዊ የፖለቲካ መረጋጋትና ጠንካራ አንድነት መፍጠር

02 በቀጠናው ያለን ይዞታ ማጠናከር

03 በቀይ ባህር ላይ የሚኖረን ሚናም መጨመር

04 ከቀንዱ ሀገራት ጋር ትብብርና ሰላም እጅጉን ማጠናከር

05 የአለም አቀፍ የግንኙነት ሚዛናችንን ጠብቀን መጓዝ

06 እድሎችን ፍጥነትና ፈጠራ አክለን ወደ ጥቅም መቀየር

# 1.2 የመንግስት ኃይል መሸርሸር

- የዚህ ዘመን መንግስታት ኃይልና ስልጣን እጅጉን ቀንሷል፤ ሽሚያ በዝቷል፣
- ኢኮቴ ተጽእኖ ፈጣሪ ነው፤ ሚስጢር በቀላሉ ይገኛል፣ ይባክናል፣
- የዲጂታል ሉዓላዊነት ትርጉም አልባ ሆኗል፣
- የትላልቅ ኩባንያዎች ዓለም አቀፍ ተጽእኖ አይሏል፣
- የዴሞክራሲ ስርዓት ያልተማከለ ኃይልና ስልጣንን እየፈጠረ ነው፣

- የጦር ኃይሎች፣ ሚዲያዎችና የእምነት ተቋማትም የሃይል መበተን ችግር ገጥሟቸዋል፣
- ዓለም ፍፁማዊ የሐሳብ ለውጥ ምህዋር ውስጥ ገብታለች። የሕዝብ ግራ መጋባት ይታያል፣
- ነፃነት፣ እኩልነት፣ ሀብት ማፍራትና የመበልፀግ እድል የዚህ ዘመን የፍጎት መገለጫዎች ናቸው፣
- አለመግባባትና ውጥረት የእለት ተእለት እውነታዎች ናቸው።

# 1.3 የድህረ እውነት ፖለቲካዊ ሐሳዊነት (HYPOCRISY)

- የድህረ እውነት ፖለቲካ ሰዎች ከሐቅ ይልቅ በስሜት የሚመሩበት፣ ከእውነትና ማስረጃ ይልቅ ወሬን ማናፈስና ስሜትን መያዝ የበላይነት የያዘበት፣ የሴራ ትንተና የብዙዎችን ቀልብና አስተሳሰብ የሚገራበት ጊዜ ነው፣
- ውስብስብ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብና የባህሪ ለውጥን ያመጣ ኑባሬ ሆኗል።
- እውነትንና ምክንያታዊነት በመያዝ ብቻ የሰውን ሀሳብና እይታ መቅረጽ የማይቻልበት፣ ከሃሳብ ጥራት ይልቅ የስርጭት አቅሙና ስሜት ኮርኳሪነቱ የበለጠ ተጽእኖ የሚፈጥርበት ዓለም ነው፣
- የውሸት ዜና፣ የተዛባ መረጃ፣ ሴራና ፕሮፖጋንዳ መንዛት፣ የተሳሳተ መረጃ ያልተገባ መረጃ፣ ወዘተ በስፋት ይታያል፣

# 1.3 የድህረ እውነት ፖለቲካዊ ሐሳዊነት …

- የመረጃ ቴክኖሎጂ ቦታና ጊዜ የሚባሉ ጉዳዮችን ማጥበቡና ማሳጠሩ፣
- የተደራጀ ተቋማዊ ባህል ያላቸው እንደነ አሜሪካ  የመሳሰሉትን ጭምር በብርቱ የፈተነ፣
- በሀገራችንም ካለን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ ብዝሃነት አኳያ ቡድንተኝነትን አወሳስቧል፣
- የአውሮፓ የሰላም ኢንስቲትዩት በ2021 ባደረገው የዳሰሳ ጥናት በማህበራዊ ሚዲያ የግጭት አጀንዳ የነበሩ ዋና ዋና ጉዳዮች በብሔር ማንነት፣ ፌደራሊዝምና ብሔርተኝነት፣ ህዳሴ ግድብ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ናቸው።
- የግጭት፣ የነውጥ እና የጥላቻ መረጃዎችን የሚያሰራጩ አካላት የበለጠ ተቀባይነት አግኝተው በርካታ ተከታይ አፍርተዋል።

# 1.3 የድህረ እውነት ፖለቲካዊ ሐሳዊነት …

- በዚህ የድህረ እውነት ዓለም ውስጥ እንዴት ታግለን እውነታችንን ሕዝባችን ጋር እናደርሳለን? ትልቅ አጀንዳችን ሊሆን ይገባል፣
- የመረጃ አቅም የሌለው አካል የፖለቲካ አቅም ሊኖረው አይችልም፣
- የአጭር ጊዜ መፍትሄ የሐሰት መረጃ አሰራጮች የመመከትና የመልሶ ማጥቃት ርምጃዎችን መውሰድ፣
  - ✓በቂ መረጃና ማስረጃ መያዝ፣
  - ✓ማሰልጠን፣ ማጣመር፣ የዓላማና የተግባር አንድነት መፍጠር፣
- ከረጅም ጊዜ አኳያ ተዓማኒነት ያለው ጠንካራ፣ ተደራሽና የተደራጀ ሀገራዊ የሚዲያ ተቋም ግንባታ ወሳኝ ነው።

## የኃይማኖት፣ የብሔርና የፖለቲካ ጽንፈኝነት ጥምረት አደጋ፣

የሀገራችን ፖለቲካ አንዱ ጉድለት የጋራ አጀንዳን በመፍጠር ህዝብን ለጋራ ግብ ማሰባሰብ አለመቻሉ ነው፣

ሁሉም ራሱን የእውነት ብቸኛ ባለቤት አድርጎ ይመለከታል፣

በተለያዩ አስተሳሰቦች፣ አመለካከቶችና ማንነቶች መካከል መስተጋብር አለመፍጠርና የጋራ አጀንዳ ይዞ መታገል አለመቻል የፖለቲካችን አንዱ ትልቅ ክፍተት ሆኖ ሲፈትነን ቆይቷል፣

# አክራሪነት

- ልዩነትን ያለ አግባብ ለጥጦ መመልከት፣ ማናቸውንም ዓይነት የልዩነት ሃሳቦችን ለማድመጥም ይሁን ለማክበር ፍላጎት የማጣት የፖለቲካ አካሄድ ነው፣
- አክራሪነት ሰፍኗል ልንል የምንችልባቸው 2 ጉዳዮች መንታ ሆነው ሲመጡ ነው።

1. ልዩነቶችን አላግባብ በመለጠጥ እውነት የእኔ ብቻ ነው ማለትና ስለሌላው ያለው እይታ ማቻቻል የሌለበት ወይም የበላይነትን መፍጠር እና ማጥፋት የሚተልም ሲሆን
2. ሐሰት የሚሉትን ከእነርሱ ውጭ ያለውን አመለካከት ለማጥፋት ማንኛውንም አይነት ኃይል እና ማጥቃትን እንደ መንገድ የሚጠቀም ሲሆን ነው።

# አክራሪነት…

- ልዩነትን ያለ አግባብ ለጥጦ መመልከት፣ ማናቸውንም ዓይነት የልዩነት ሃሳቦችን ለማድመጥም ይሁን ለማክበር ፍላጎት የማጣት የፖለቲካ አካሄድ ነው፣

- አክራሪነት ሰፍኗል ልንል የምንችልባቸው 2 ጉዳዮች መንታ ሆነው ሲመጡ ነው።

1. ልዩነቶችን አላግባብ በመለጠጥ እውነት የእኔ ብቻ ነው ማለትና ስለሌላው ያለው እይታ ማቻቻል የሌለበት ወይም የበላይነትን መፍጠር እና ማጥፋት የሚተልም ሲሆን
2. ሐሰት የሚሉትን ከእነርሱ ውጭ ያለውን አመለካከት ለማጥፋት ማንኛውንም አይነት ኃይል እና ማጥቃትን እንደ መንገድ የሚጠቀም ሲሆን ነው።

# አክራሪነት...


- የእኛ እና የእነሱ ወገን ብሎ በመለየት የአንዱን ወገን በሌላው ላይ መቀስቀስ፣ ማነሳሳት እና ማስጠቃት እንደ ማስፈፀሚያ መንገድ ይጠቀማል፣
- ጫፍና ጫፍ ያሉ አመለካከቶችን ወደ አማካይና ወደ አስታራቂው መስመር የማምጣት ፍላጎት አለመኖር፣
- ለውይይት፣ ለክርክር እና ለመቀራረብ ቦታ አለመስጠት፣
- የጥላቻ ትርክት በፍጥነትና በብዛት ታች ድረስ ማሰራጨት፣
- አሉታዊ ትርክትና ጽንፈኝነት በቀላሉ መስፋፋት፣

# አክራሪነት የሚያስከትላቸው የሀገረ መንግስቱን ጥንካሬ የሚፈትኑ ችግሮች

## 1. የወል እውነት (የጋራ ግብ) መላላት፡-

ያልተገባ ውድድር እና ግጭት ይፈጥራል፣

የጋራ ግብ የህዝብን የጋራ ዕጣ ፈንታ የተሻለ ማድረግ ነው፣




በልሂቃን እና በህዝቡ ውስጥ የተፈጠረው የፖለቲካ ድባብ ትኩረቱ ተናጠላዊ ፍላጎ (ከሀገራዊ ግብ ይልቅ ቡድናዊ/ግለሰባዊ) ሆኗል።

በህብረትና በጥንካሬ በጋራ ግብ ዙሪያ መስራት ህዝብ የተሻለ ነገን እንዲያገኝ ይረዳል፣

# አክራሪነት የሚያስከትላቸው የሀገረ መንግስቱን ጥንካሬ የሚፈትኑ ችግሮች
## 2. ማህበረሰባዊ ትስስር መላላትና አለመረጋጋት

1 አንድን ስርዓት ስርዓት የሚያደርገው በማህበረሰቦች መካከል የሚኖር ትስስር ነው።

2 በተናጠላዊ የቡድን ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለ አክራሪነት ለዘመናት የቆየና የተሰራ የማህበረሰብ ትስስር ከሚሸረሽሩ ጉዳዮች መካከል ነው።

3 በሴራ ትንታኔ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ በማህበረሰብ ውስጥ መተማመንን ይሸረሽራል።



# አክራሪነት የሚያስከትላቸው የሀገረ መንግስቱን ጥንካሬ የሚፈትኑ ችግሮች
# 3. የሕግ የበላይነት እና የፖለቲካ ተጠያቂነት መሸርሸር

ስራዎችና ውጤቶች በህግ ሳይሆን በማንነት መሰረት ሲዳኙ የፖለቲካ ተጠያቂነት ይሸረሽራል፣

ከህዝብ ጋር የሚኖር ግንኙነት ግለሰባዊ ሲሆን ህጋዊና ተቋማዊ በሆነ መንገድ ተጠያቂነትን ለማምጣት ያስቸግራል። በማንነት የተቃጣ ተደርጎ ይወሰዳል።

# አክራሪነት የሚያስከትላቸው የሀገረ መንግስቱን ጥንካሬ የሚፈትኑ ችግሮች
# 4. ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በር መክፈት፣

በፖለቲካና ኢኮኖሚ አቅም ጠንካራ የሆኑ ሀገራት በውስጥ ጉዳይ በረቀቀ መንገድ ገብተው የፖለቲካ ገበያውን ለመዘወር እድል ያገኛሉ።

# 1.5 ድህነት እንደ ታላቁ ተግዳሮት

ድህነት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ነው፣

ድህነት የፖለቲካ አለመስከን፣ የሀገራት አለመረጋጋት፣ የሰላም እጦት፣ ወዘተ ያመጣል፣

ድህነት የደካማ ስርዓት ውጤት ነው፣

ኢትዮጵያ ከድህነት ለመውጣት ትክክለኛ መስመር ውስጥ እንዳለችና በ2028 ዓ.ም 3% በታች ድሃ ካለባቸው አገራት ተርታ እንደምትሰለፍ መረጃዎች ያሳያሉ።

# 1.5 ድህነት እንደ ታላቁ ተግዳሮት…

በቀጣይ በኢኮኖሚው ላይ ብቻ ሳይሆን በስርዓት አልበኝነት ላይ የራሱን አሉታዊ አሻራ እያሳረፈ ያለውን የወጣት ስራ አጥነት ችግር መቅረፍ ወሳኝ ነው፣

በየአመቱ 2 ሚሊየን አዳዲስ ስራ ፈላጊ፣ በየአመቱ 150 ሺህ ተመራቂ ተማሪ፣ ወደ አዲስ አበባ የሚደረግ ፍልሰት እና የጽንፈኛ ኃይሎች ወጥመድ ውስጥ የሚገቡ ወጣቶች መበራከት ይታያል፣

# የድህነት መፍትሔው

የመንግስትና የግል ዘርፉን ትብብር ማሳደግ፣

የስርዓት ስብራትንና የምርታማነት ችግርን መቅረፍ፣

ሁሉም ክልሎች ተቀራራቢ የሆነ እድገት እንዲኖራቸው መስራት፣

# 1.6 በእንጥልጥል ላይ ያለ የሀገር ግንባታ

## ሀገራችን የረዥም ጊዜ የሀገርነት ታሪክ ቢኖራትም ለአንድ ሀገር ጥንካሬ መሰረት የሆኑ ከሚከተሉት መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች አንፃር ሰፊ ክፍተት አለባት

01 የነፃና ብቁ ተቋማት አለመገንባት

02 የጋራ ማንነት ለመገንባት

03 መፃኢውን ትውልድ በኢትዮጵያዊነት የመቅረጽና የማነጽ ችግር

04 ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት

# 1.6 በእንጥልጥል ላይ ያለ የሀገር ግንባታ…

- የሽግግር ወቅትን ማዕከል ያደረገ የግጭትና የኃይል አሰላለፍ ሀገረ መንግስቱን እየፈተነ ነው፣

  @ የብሔርና የኃይማኖት ግጭት መቀስቀስ ፖለቲካዊ ግድያዎች፣ መፈናቀልና ከፍተኛ የንብረትና የሀብት ውድመት፣ ወዘተ

- የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የተቋማት ደካማነት፣ የኢኮኖሚ አቅም አለመዳበር፣ ሌብነት እና የግጭቶች መበራከት፣ ዘላቂና ተግባራዊነቱ አጠያያቂ ያልሆነ መንግስት ለመመስረት እንቅፋት እየሆኑ ይገኛሉ።

- በሀገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል በመሰረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ማለትም በታሪክ፣ በህገ መንግስት፣ በሰንደቅ አላማ፣ በፌዴራሊዝ፣፣ በወሰንና በማንነት፣ ወዘተ ጉዳዮች ዙሪያ መግባባት የለም።

- በዚህም የሀገራችን ህልውና አደጋ ውስጥ ገብቷል፣

- የሀገር ግንባታ ሂደቱን በጽኑ መሰረት ላይ ለማቆም ብሔራዊ መግባባትን መፈጠር ያስፈልጋል፣

- ሀገራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊ አዝማሚያዎች ጋርተያያዞ የተፈጠሩ እድሎችን መጠቀም እንዲሁም ተግዳሮቶችን መግታት ያስፈልጋል

# ክፍል ሁለት

# የፈጠራና ፍጥነት አስፈላጊነት

# 2.1 ኋላ ከቀረንበት ወጥተን ከፊት ለመገኘት

# በለውጥ ጉዟችን ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ አዝማሚያዎች

- ሀገራዊ ችግሮቻችን ስር የሰደዱ፣ አንዱ ከአንዱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የችግር አዙሪትን የሚፈጥሩ መሆናቸው፣

@የደካማ ተቋማት ተጽእኖ፣ በፍጥነት እየተለዋወጠ የመጣው ዓለም አቀፍ ሁኔታ እድሎችን እና አደጋዎችን ይዞ መምጣቱ፣

@ከችግሮቹና ከፈተናዎቹ በልጠን ለመጓዝ የሚያስችል ፍጥነት ሊኖረን ይገባል፣

@ሰፊና ብዙ አቅም ይዘን አቅማችንን ለመጠቀም የሚያስችል ፍጥነትና ፈጠራ ማዳበር ካልቻልን አስቸጋሪ ይሆናል።

@አቅማችንን የምንጠቀምባቸው እና ችግሮቻችንን የምንፈታባቸው አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት እና ተግባራዊ የማድረግ ስራ መስራት፣

@ብልጽግና የወረስናቸውን ውዝፍ ችግሮች የማቃለል እና ለትውልድ የሚተርፍ ትሩፋት የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፣

@በፓርቲና በመንግስት መዋቅር ውስጥ ፈጠራና ፍጥነት እንደ ግልና እንደ ቡድን ምን ያክል አለን? የሚለውን መፈተሽ ያስፈልጋል፣

@ፍጥነት በውስጡ ጊዜና ርቀትን ይዟል፣

@ፈጠራ ከራዕያችን ለመድረስ አማራጭ የሚያቀርብ መሳሪያ ነው።

# 2.2 ጊዜና የምርጫ ቃል ኪዳን

01

በውክልና ዴሞክራሲ ውስጥ መራጩ ተመራጩን ውክልና የሚሰጠው በምርጫ ቃል ኪዳኑ ላይ የተቀመጡትን ግቦች እንዲያሳካለት ነው።

02

ቃል ኪዳን ተጠያቂነትን ያመጣል።

03

በቀጣይ የምንመዝነው ከፖሊሲ አማራጮች በላይ በተግባር ስኬቶቻችን ይሆናል።


04

ቃላችንን በጊዜ ገደቡ ለመጠበቅ በምን ፍጥነት እየተጓዝን ነው? በቂ ነው ወይ? የሚለውን መፈተሽ ይኖርብናል።

05

አሁን ያለብን ዋናው ጥያቄ የፍጥነት ጥያቄ ነው።

# 2.3 ቃልን ማጠፍ እና ቃልን ማክበር




ቃልን ማጠፍ እምነትን የሚሸረሽርና እንደ ከሐዲ የሚያስቆጥር የፖለቲካ ባህልን የሚጎዳ ነው።

ብልጽግና ቃሉን ጠብቆ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት በማስመዝገብ የዴሞክራሲ ባህል ለውጥ ለማምጣት ይተጋል።

ቃሉን የሚጠብቅ እና ለህዝብና ለራሱ ታማኝ መሆኑን የሚያስመሰክር የፖለቲካ ጥራትና ቁርጠኝነት ያለው ፓርቲ ነው ብልጽግና፣

ሆኖም የርምጃችን ልክነት ብቻ ሳይሆን የርምጃችን ፍጥነት እጅግ ወሳኝ ነው።

# ክፍል ሶስት

# የመፍጠን ጅማሮ ስኬቶች

# 3.1 ብልጽግናዊ መንግስት እና ኢኮኖሚያዊ ፍጥነት

- የአንድ ማህበረሰብ እድገትና ለውጥ ማህበረሰቡ ባለው እምቅ አቅምና በፈጠረው ስርዓት ላይ ይመሰረታል።

- በሀገራችን ሕዝብ በድህነት የሚማቅቅበት ዋነኛ ምክንያት ለመበልፀግ የሚያስችል አቅም ሳይኖረን ቀርቶ ሳይሆን እምቅ አቅሞችን ተጠቅሞ ለህዝብ ተድላና ሐሴት መፍጠር የሚችል ስርዓት ባለመገንባታችን ነው።

- ስርዓት ሲባል የተለያዩ ተዋንያን እና ንዑሳን ስርዓቶች ድምር ሲሆን እነዚህን ንዑስ ስርዓቶችና ተዋንኒያን በሚገባ ሚናቸውን የሚወጡ መሆን አለባቸው።

- የህዝብ ፍላጎት በየጊዜው የሚለዋወጥ እና የሚያድግ ነው። ነገን የተሻለ ለማድረግ አልመን እየሰራን ነው።

# 3.1 ብልጽግናዊ መንግስት እና ኢኮኖሚያዊ ፍጥነት...

- በሀገራችን ምርታማነት ለማረጋገጥና ሀብት ለመፍጠር አዳዲስ መንገድ፣ ፍጥነትና ቅልጥፍና ያስፈልጋል፣
- የሀገራችን መሰረታዊ ችግሮች አንዱ አቅሞቻችንን በሚገባ አለመረዳታችን ነው፤
- ሌላው ከፍ ያለ ውጤት ሊሰጥ የሚችል አዲስ ምልከታ እና አዳዲስ ፈጠራ ችግር ነው፣
- በፍጥነት ማሰብ፣ በቶሎ መተግበር እና ማጠናቀቅ ወሳኝ ናቸው፣

- መፍጠንና መፍጠር ስጋቶችን ወደ እድል ለመቀየር አስችለውናል።

@GDP በ2014 126.8 ቢሊየን ዶላር መድረሱ፣

@ባለፉት 4 አመታት በአማካይ 7.1% እድገት ማስመዝገባችን።

@ከአፍሪካ 5ኛ ኢኮኖሚ ከአለም ደግሞ 59ኛ መሆን መቻላችን፣

@ነፍስ ወከፍ ገቢን 1,218 ዶላር ማድረስ መቻላችን፣

# 3.1 ብልጽግናዊ መንግስት እና ኢኮኖሚያዊ ፍጥነት…

- በነጠላ ቡድናዊ ተጠቃሚነት የበላይነት ሲዘወር የነበረን ኢኮኖሚ፣ ለሁሉም ፍትሃዊ እና እኩል ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጥ ለማድረግ ታግለናል።
- ነገር ግን አዲስ መንገድ፣ አዲስ እይታንና አዲስ አስተሳሰብን ለመቀበል ጊዜ ይወስድብናል።
- በቀጣይ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ አዲስ ፈጠራዎችን መጠቀም፣ ማህበረሰቡን ከሸማችነት ወደ አምራችነት መቀየር፣ የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት፣ የሌማት ትሩፋት በሽፋን፣ በጥራትና በምርት ማሳደግ፣ የማዕድ ማጋራት እና የምገባ ስራዎችን በሁሉም ክልሎች ማስፋት፣ የግብርና ምርምሮችን ማስፋትና ለምግብነት የሚውሉ ምግቦችን ወደ ገበያ በብዛት ማስገባት፣ ሰላም ማስከበር እና የአቅርቦት ጉድለትን በመሙላት የኑሮ ውድነት የፖለቲካ ነጋዴዎች አጀንዳ እንዳይሆን ልንሰራበት ያስፈልጋል።

# 3.2 ከተናጠል ወደ ወል እውነት

- እውነት ፍፁማዊ፣ አንፃራዊ እና ተጨባጭ በሚል በ3 ይከፈላል፣
- የተናጠል ቡድናዊ እውነታ
  - ✓ሁሉንም የማስተግበሪያ አቅሞች ተጠቅሞ በሀይል ይጭናል።
  - ✓ገኸ ትርክት መፍጠር እንደ ዋነኛ መሳሪያ፣
  - ✓ሌላውን ማግለል፣ መፈረጅ እና ማጥላላት እንደ ስትራተጂ፣
  - ✓የሌላውን እውነት ለማካተት አለመፈለግ መገለጫዎቹ ናቸው፣

# 3.2 ከተናጠል ወደ ወል እውነት…

- ብልጽግና ያለፉ ስርዓቶች የተናጠል ቡድናዊ እውነትን ገዥ የማድረግ ፍላጎት ወደ ጎን በመተው "በመደመር" አዲስ ሀገር በቀል እሳቤ እውነተኛ ህብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ለመገንባት የሁሉም እውነት ዋጋ ወደሚያገኝበት ወደ ሁለንተናዊ የወል እውነት መሻገር እንደሚያስፈልግ በጽኑ ያምናል።

# 3.2 ከተናጠል ወደ ወል እውነት…

- ለዚህም ወንድማማችነትንና እህትማማችነት ማዕከል ማድረግ ወሳኝ መሆኑ ያምናል፣
- የአመለካከት ጥራት መፍጠር፣ የአሰላለፍ ግልጽነት ማምጣት፣ የአቋም ጽናት ማረጋገጥ፣ የዓላማ ቁርጠኝነት መመስረት እና አደረጃጀቶችን በሙሉ አቅማቸው ወደ ተግባር ማስገባት አስፈላጊ ነው፣

# 3.2.1 የወል እውነቶችን የማጽናት ፖለቲካዊ እምርታችን፣

- ብልጽግና ሀገራዊና ብሔራዊ ማንነቶች በልከኛው ቦታቸው ላይ እንዲቀመጡ ሰርቷል፣
- ወንድም/እህትማማችነትን፣ አካታችነትንና ህብረ ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ ስራዎች ባለፉት 5 አመታት ተከናውዋል።
- ፓርቲያችን የወል እውነቶች የበለጠ ፖለቲካዊ ገዥ እሳቤዎች እንዲሆኑ እየሰራ ይገኛል።
  - ✓አካታችና አቃፊ ጠንካራ ፓርቲ መቋቋሙ፣
- ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ ዴሞክራሲያዊ መብት በሚገባ ለማስተናገድ ፓርቲያችን ብዙ ስራ ሰርቷል።
- ሀገራዊ ሰላም በማረጋገጥ ጦርነትን የማስቀረት ስራ ሲሰራ ቆይቷል።

# 3.2.1 የወል እውነቶችን የማጽናት ……

- የሀገረ መንግስት ግንባታ ቀሪ ስራዎችን ለመፈፀም የሚከተሉትን ወሳኝ ተግባራት መፈፀም፣
  - ✓የህግ የበላይነት እና ህገ መንግስታዊነት ማረጋገጥ፣
  - ✓የሀይል አጠቃቀም ማዕከላዊነት ማረጋገጥ፣
  - ✓የፀረ ሙስና ትግላችንን ማጠናከር፣
  - ✓የአመራርነትና አባልነት ግዴታዎቻችንን በብቃት መወጣት፣
  - ✓በአጀንዳ የበላይነት የጥላቻ ፖለቲካን ማዳከም፣
  - ✓እነዚህን በብቃት፣ በፍጥነትና በቆራጥነት በማከናወን ተጨማሪ ውጤቶችን ማስመዝገብ ይጠበቅብናል።

# 3.2.2 ዘላቂ ሰላም የማረጋገጥ ርምጃችን

- ፓርቲያችን የሰላም አርበኛ ነው፣

- በሀይል የሚፈፀም የነጠላ ቡድናዊ ፍላጎት እንደማይኖር አረጋግጧል፣

- የተሃድሶ ኮሚሽኑን ማጠናከር፣ በተባበረ የህዝብ እና የፓርቲ አቅም የወደሙትን መልሰን መገንባት እና ሰላማችንን ማዝለቅ ይኖርብናል፣

- ሰላማችንን ዘላቂ ለማድረግ፣ ቂምን ለመሻር፣ ከሂሳብ ማወራረድ የጥላቻ መንገድ ለመውጣት የሚያስችል ፍትህን ማረጋገጥ፣ የሽግግር ፍትህ ማሕቀፍን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፣

- የፀጥታ ተቋሞቻችንን የላቀ ማድረግ፣ የንግግር ጠረጴዛዎቻችንን መርህን ለጠበቁ ንግግር ማዘጋጀት እና የተሟላ ሀገራዊ ሰላም ለማረጋገጥ መርህን መሰረት ያደረገ ስራ መስራት ያስፈልጋል።

# 3.2.3 የህግ የበላይነት ለፖለቲካዊ እምርታችን ቀጣይነት

- ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ 3 መሰረታዊ የስጋት ምንጮች ትኩረት ይሻሉ፣

1. ካለንበት የፖለቲካ ሽግግር የሚመነጭ ሽኩቻ

✓የዴሞክራሲ ባህል አለመዳበር፣ ስር የሰደደ የሴራ እና የሸፍጥ ፖለቲካ ልምምድ፣ ነፃነትን በአግባቡ ከኃላፊነት ጋር አመዛዝኖ የመጠቀም ልምድ አለመኖር ደራርበው መጥተዋል።

✓የህግ ማስከበርና ተጓዳኝ ርምጃዎችን መውሰድ ወሳኝ ነው፣

# 3.2.3 የህግ የበላይነት ለፖለቲካዊ እምርታችን ቀጣይነት …


## 2 ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት እና አመክንዮ ያላቸው ወንጀሎች

ሙስና፣ ሌብነት እና የመንግስትና የህዝብ ሀብት ምዝበራ ብቻ ሳይሆኑ ኮንትሮባንድ፣ ህገ ወጥ ንግድ፣ በጦር መሳሪያ፣ በአደንዛዥ እፅ እና በሰው ልጆች ላይ የሚደረግ ንግድ፣ ከፋይናንስ ጋር የተገናኙ ወንጀሎች ይታያሉ፣

ወንጀል ፈፃሚዎች የህግ አስከባሪ መዋቅሩን ለማሽመድመድ ጥረት ያደርጋሉ፣

ቀስ በቀስም የፖለቲካ ክንፍ በመፍጠር ለሀገር ደህንነት ትልቅ ስጋት ይደቅናሉ።

ስለሆነም የፍትህ ሪፎርሙን ማጠናከር ወሳኝ ይሆናል፣



# 3.2.3 የህግ የበላይነት ለፖለቲካዊ እምርታችን ቀጣይነት ...

## 3. የሙስና ትግሉን ማጠናከር

01 የፍትህ ተቋማት ተቀራርቦ መስራት፣

02 የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣

03 በፓርቲ መሪነት የፀረ ሙስና ትግላችን ማፋፋም፣

04 የነፃነት አስተዳደር እና አጠቃቀም በህግ አግባብ ሚዛን መጠበቅ፣.


# 3.2.4 የኃይል አጠቃቀም ማዕከላዊነት

- በዘመናዊ የሀገረ መንግስት ግንባታ ቁልፍ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ መንግስት በብቸኝነት ኃይልን የመጠቀም መብቱን ማስከበሩ ነው።
    - ✓በሀገር ወስጥ ህግና ስርዓትን ማስከበር፣
    - ✓ሀገርን ከወረራና ከውጭ ጠላት መከላከል
- በወታደራዊ ሳይንስና መርሆዎች መሰረት በተማከለ ሁኔታ ኃይልን ማደራጀት የወል እውነት ገዥነት እንዲመሰረት ፋይዳው የላቀ ነው።

# 3.2.5 የህገ መንግስት ቅቡልነት የወል እውነትን ማጽኛ መሰረት

በዘመናዊ የህገረ መንግስት እና የፖለቲካ ስርዓት፣ ህገ መንግስት ትልቅ ቦታ አለው።

ህገ መንግስት በአንድ ሀገር ውስጥ ካሉ ከሌሎች ህጎች የተለየ፣ እጅግ ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠው የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነ ህግ ነው።




በአጠቃላይ የአንድ ሀገር ፖለቲካዊ እና ህጋዊ ስርዓት የሚዋቀረው እና የሚመሰረተው በህገ መንግስት ላይ ነው።

ህገ መንግስቱን በዘመናዊ አስተሳሰብ ልዩ የሚያደርገው በህጎች ተዋረድ ባለው ከፍተኛ ስፍራ ብቻ ሳይሆን በይዘቱም ጭምር ነው።

ህገ መንግስቶች የሚሻሻሉበት ሂደት ከመደበኛ የህግ አወጣጥ ስርዓትና ከሌሎች ህጎች የተለየ እና ጠበቅ ያለ በመሆኑ ለመለወጥ አስቸጋሪ ነው።

ዘመን ተሻጋሪ፣ ቋሚ እና መዋቅራዊ ጉዳዮችን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ይዟል።

# 3.2.5 የህገ መንግስት ቅቡልነት የወል እውነትን ማጽኛ መሰረት…

- በህገ መንግስቱ ላይ የሚነሱ ውዝግቦች ካልተፈቱ በሀገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግና ማረጋገጥ አዳጋች ነው። የወል እውነቶች ገዥ የሚሆኑበት ጠንካራ ሀገረ መንግስት ለመገንባትም አይቻልም።
- ፓርቲያችን ህገ መንግስቱ የሁላችን የሆኑ የወል እውነቶችን ገዥ ሃሳቦች ያደረገ፣ በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ቅቡልነት ያለው እና የሀገራችንን ቀጣይ እጣ ፈንታ ታሳቢ ያደረገ ሰነድ መሆን እንዳለበት ያምናል።
- በህገ መንግስቱ ዙሪያ የጋራ አመለካከትና ሀገራዊ መግባባትን መገንባት ያስፈልጋል።
- ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ህገ መንግስቱን ጨምሮ ያልተቋጨውን የሀገረ መንግስት ግንባታችንን መስመር የምናስይዝበት ነው።

# 3.2.6 የውስጠ ፓርቲ አንድነት ለርዕያችን ስኬት

- የብልጽግና ፓርቲ መመስረት የወል እውነቶችን ገዥ ስርዓት እንዲሆን የማድረግ ፍላጎታችን ውጤት ነው።
- በዋነኝነት የውስጠ ፓርቲ አንድነት ፈተና የሆነው የነጠላ ቡድናዊ እውነታቸው ገዥ እሳቤ እንዲሆን የሚፈልጉ ኃይሎች በውስጣችን በመኖራቸው ነው፤
- አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የድሉም የውድቀቱም ምንጭ የአመራር እና የአባሉ አመለካከት ነው።
- አመራራችን ቀውሶችን ማስተዳደር የሚችል ብዝሃነትን ከልቡ የተቀበለ፣ የገዥ ፓርቲ አመራር ስነ ልቦና ያለው፣ ወቅታዊ የፖለቲካ አሰላለፎችን የሚረዳ፣ ጂኦፖለቲካዊ ግንዛቤ ያለው፣ አዳዲስ ሃሳቦችን በማመንጨት ችግር ፈቺ የመሆን አስተሳሰብ ደረጃ ላይ የደረሰ፣ የወል እውነቶች ገዥ ሃሳብ እንዲሆኑ እሰራለው ብሎ የቆረጠ እና የሰፈሩ ጉዳይ ሲነሳ ለሰፈሩ ጠበቃ ለመሆን ወደ ሰፈር አስተሳሰብ የማይወርድ አመራር መፍጠር የወል እውነቶችን ገዥ የሆኑባት ሀገር የመገንባት ራዕያችንን እናሳካለን።

# 3.2.6 የውስጠ ፓርቲ አንድነት ለርዕያችን ስኬት…

- የፓርቲ አደረጃጀቶች ዋነኛ የፓርቲ ተልዕኮ የመፈፀሚያ መሳሪያዎች ናቸው።
- የውስጠ ፓርቲ አንድነት በ3ቱ አእማዶች ስምረት የሚፈጠር ነው።
- በአመለካከት፣ በአሰላለፍ እና በአደረጃጀት ስምረት
  - ✓እነዚህን መሰረት በማድረግ መገምገም፣ መዛነፎችን በፍጥነት መሙላት፣ በድጋፋዊ ስልጠና ማብቃት፣ ባለማቋረጥ የንድፈ ሃሳብ መጽሄት ማዘጋጀት፣የአደረጃጀቶቻችንን የማድረግ አቅም ማሳደግ፣ የህዋሳት ግንኙነት ማጠናከር፣ የመንግስት ተቋማት አደረጃጀቶችን ዋነኛ የተልዕኮ መፈፀሚያ ማእከሎች እንዲሆኑ ማነቃቃት፣ የአመራርና አባላት ምዘና በተጨባጭ ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን ማድረግ፣ ሌብነትን የመከላከል ተግባራችን ከአመለካከት ጀምሮ የአመራርና የአባል ተጠያቂነትን እያሰፈነ መሄድ ይገባዋል።
  - ✓የአጀንዳ ሰጪነት የበላይነት መያዝ፣
- ከአመለካከት ጥራት እስከ አጀንዳ ሰጪነት የተደራጀ ተልዕኮ የውስጠ ፓርቲ አንድነትን ለማስጠበቀ ወሳኝ ነው፣

# 3.3 የታደሰው የዓለም አቀፍ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ

- ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷ በገለልተኝነት (NON ALIGNED) መርህ ላይ ላይ የቆመ ነው።
- የአንድ ሀገር የዲፕሎማሲ ጥንካሬ ቁልፍ መገለጫ ውስጣዊ ጥንካሬና አንድነት ነው።

3.3.1 የሰሜኑ ግጭትና የዲፕሎማሲያችን ፈተና፣

- በሪፎርም የሰመረውን ዲፕሎማሲ ወደ ኋላ የመለሰ፣
- የሀገራችንን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ጭምር ፈተና ውስጥ የከተተ ክስተት ነበር።
- ግጭቱ በ3 መንገዶች ዲፕሎማሲያችንን ክፉኛ ጎድቶታል።
  - ✓በመረጃ ጦርነት ብልጫ ተወስዶብን ስማችንን አጠለሸ፣
  - ✓የርዳታና የመንግስት የበጀት ድጎማን የማስቀረት ርምጃ አስከተለ፣
  - ✓የውጭ ኃይሎች በተዘዋዋሪ መንገድ ለተቃራኒ ወደረኞች ድጋፍ ማድረግ፣

# 3.3 የታደሰው የዓለም አቀፍ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ…

## 3.3.2 የፕሪቶሪያው የግጭት ማቆም ስምምነት አዲስ ምዕራፍ፣

- ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሂዎች አቅጣጫ መከተላችን ውጤታማ አድርጎናል፣

## 3.3.3 ማስገንዘብና ማለዘብ (RE-ENGAGEMENT) የውጭ ግንኙነታችንና ዲፕሎማሲያችንን ማደስ፣

- US-AFRICA ጉባኤ ተጋብዘን መሳተፋችን፣
- የጀርመን፣ ኢጣሊያ፣ ስሎቬኒያ እና ሐንጋሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉብኝት፣
- የጀርመንና የኢጣሊያን ርዕሳነ መንግስታት ጉብኝት፣

# 3.3 የታደሰው የዓለም አቀፍ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ...

## 3.3.4 ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ የኢትዮጵያ ተግባራዊ ድል፣

01

የራስን አቅም የሚያሳድግ ነው፣

02

ለአህጉራዊ ተቋም የቅቡልነት አቅም የሚፈጥር ነው፣

03

ከአካል ገዥነት ወደ አስተሳሰብና ኢኮኖሚ እስረኛነት የተቀየረውን የምዕራባዊያን አዲሱን ስትራተጂ የሚያመክን ነው፣

04

ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት ወደ ሙሉ ነፃነታቸው ለመሻገር ለሚያደርጉት ትግል የበለጠ ጉልበት ይሰጣል።


# 3.3 የታደሰው የዓለም አቀፍ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ...

## 3.3.5 የጋራ ተጠቃሚነትን ያረጋገጠ ቀጣናዊ ትስስር፣

ከጎረቤት ሀገራት ጋር በመተባበርና በመነጋገር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መመስረትና ማጠናከር፣

የጋራ ጥቅማችንን በመታጋገዝና በመተባበር ማሳካት፣

ለዚህም አካባቢያዊ የልማት፣ የኢኮኖሚ እና የሰላም ዲፕሎማዊ ትስስር መፍጠር እና ቀጠናዊ የኢኮኖሚ ጥምረት መገንባት፣



በቀጣናው ሚዛን የጠበቀ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

የታላቁ ህዳሴ ግድብ የሶስትዮሽ ድርድር በአፍሪካ ህብረት ማህቀፍ ማስቀጠል።

# ክፍል አራት

# ከፍጥነት የሚገቱን

የፓርቲና የመንግስትን
ፍጥነት የሚስቡ
ውጫዊና ውስጣዊ
አካላት አሉ።

ከፍጥነት
የሚገቱን

እኔ አይተኬ ነኝ፣ እኔ
መነካት የለብኝም፣ ከኔ
በላይ ላሳር የሚሉ
አመለካከቶች
የሚወልዷቸው
ኩርፊያ፣ ልግመኝነትና
ዳተኝነት ይስተዋላል

ከፍጥነት
የሚገቱን

ከፍጥነት
የሚገቱን

በስርዓታችን ውስጥ
ፍጥነትን እና
ፈጠራን
እንዳናረጋግጥ
ያደረጉን ከታሪ እና
አንሸራታች ኃይሎች
አሉ።

# 4.1 የሰርጎ ገብ ፖለቲካ ርዕይን መንጠቅ፣ እይታን መስረቅ

- ሰርጎ ገብንት በመጥለፍ የራስን ግብ ለማስፈፀም ወይም ፓርቲውንና መንግስትን ለማዳከም የሚደረግ ጥረት ነው፣
- የአንድ ፓርቲ ዓላማ እና ግብ ተፈፃሚነት በአመራሩ እና በአባላቱ ቁርጠኝነት ይወሰናል።
- የፓርቲያችንን ርዕይ ለመንጠቅ እና እይታውን ለመስረቅ የሚሞክሩ ኃይሎች 3 ጉዳዮችን ይጠቀማሉ፡-
  1. ከርዕያችን እና ከዘላቂ ግባችን ይልቅ በጊዜያዊ ክስተቶች እና አጀንዳዎች እንድንጠመድ እና እንድንከፋፈል ማድረግ፣
  2. ክስተቶቹና አጀንዳዎችን ተጠቅመው የተጠለፉና የተወሰዱ አመራሮችን በመጠቀም ወደ ፓርቲያችን ሰርገው መግባትና መዋቅሮችን መቆጣጠር፣
  3. በክስተቶችና በአጀንዳዎች ያልተወሰዱትን እና ያልተጠለፉትን ወይም ፀንተው የቆዩትን አመራሮች ማሸማቀቅና መግደል ነው።

# 4.1 የሰርጎ ገብ ፖለቲካ ርዕይን መንጠቅ፣ እይታን መስረቅ…

- በዓላማቸው የተሰዉ አመራሮቻችንን አደራ ተቀብለን የኢትዮጵያን ብልጽግና በማረጋገጥ ብልጽግናዋን የስማቸው መታሰቢያ ለማድረግ በቁርጠኝነት እንታጋላለን፡
- በፓርቲያችን ውስጥ በአቋራጭ ስልጣን እና ገንዘብ እናገኛለን ብለው የሚንቀሳቀሱ ኃይላት ፓርቲያችንን በመጥለፍ እና በማዳከም ስልጣንና ሀብት ለመቆናጠጥ ይንቀሳቀሳሉ።
- በአንድ በኩል የዴሞክራሲ ልምምዳችን ሳይደናቀፍ በማስቀጠል፣ በሌላ በኩል ኢ-ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ስልጣን ለመቆናጠጥ የሚደረጉ ጥረቶችን እንከላከላለን።

## 4.2 የተናጠል እውነት እና አንፃራዊ ጥቅም፤

- ብልጽግና የጋራ እውነታችን ነው።
- አንዳችን ያለአንዳችን ቀጣይነታችንን ልናረጋግጥ አንችልም። ህልውናችን የተጋመደ ነው።
- የሁላችን ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው የጋራ እውነታችንን በማጽናት ወይም ባለማጽናት ነው።
- ብልጽግናን ማረጋገጥ በጋራ መሰባሰብና በጋራ መቆምን ይጠይቃል።
- ዘላቂ ግብን ያማከለ መፍትሄ ያስፈልጋል።

## 4.3 ያልተገባ ክብርና ሀብት ፍለጋ፤

- ለብልጽግና ደንቃራ ነው።
- ቅልጥፍናን መጨመር እና መፍጠን ያልቻልንበት አንዱ ምክንያት ያልተገባ ጥቅምና ያልተገባ ክብር ፍለጋ የሚሄዱ አካላት ስላሉን ነው።
- የሌብነት ችግር የህዝብ ሀብትን ለግል ጥቅም ማዋል ብቻ ሳይሆን ነገሮችን ማወሳሰቡና ሂደቶችን ማጠላለፉ ጭምር ነው።
- ያልተገባ ጥቅም የሚፈልጉ ሰዎች በኢጎ ነው የሚመሩት። መሬት ላይ ችግሮችን ለማየት አይችሉም። ስለዚህም መፍትሄን ለማምጣት አይችሉም፤ አይፈልጉምም።
- ሌብነት ከተስፋፋ በመሪዎች መካከል የሚኖር መናበብ የላላ ይሆናል። አንዱ አንዱን ለማድመጥና በጋራ ለመስራት ክፍተት ስለሚፈጥር በቅልጥፍና እና በውጤት ረገድ ከፍተኛ ተጽእኖ ይፈጥራል። በተደራቢ ችግር ህዝብ ያለአግባብ እንዲንገላታ በማድረግ ምሬት ፈጥሯል።

# 4.4 ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን አለማዋለድ፤ ጠባቂነት እና መርህ አልባነት

- ለመፍጠንና ለመፍጠር ፈተና ከፈጠሩብን ጉዳዮች አንዱ አዲስ ሃሳብ እና አዲስ ባህል ለመላመድ ያለን ዝግጁነት አዝጋሚ መሆኑ ነው።
- ብልጽግና አዲስ ሃሳብ እና አዲስ ባህል እያስተዋወቀ ያለ ፓርቲ ነው። የተለየ የአሰራር ስርዓትና አዲስ የፖለቲካ ልምምድ ይዞ የሚንቀሳቀስ ነው።
- የዴሞክራሲያዊ መርሓዊነት እና የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን የመላመድ እና ለዚያ ተገዢ የመሆን ችግር ይታያል።
- ፓርቲያችን ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን በውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ ተክቶታል።
- ይህንን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የጠባቂነት ስሜት ትልቅ ክፍተት ሆኗል።

# 4.4 ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን አለማዋለድ…

- ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን ባለመረዳትም ሆነ ሆን ተብሎ መርህ አልባነት ተፈጥሯል።
- ፓርቲን ፓርቲ የሚያደርገው ስነ ስርዓት (ዲሲፕሊኑ)፣ ዴሞክራሲን ዴሞክራሲ የሚያደርገው መርሆዎቹ ናቸው።
- የስነ ስርዓት እና የመርህ አለመከበር ፓርቲውንም ዴሞክራሲውንም አደጋ ላይ ይጥላሉ።
- ዴሞክራሲያዊ መርሐዊነት የ2 ነገሮች ውቅር ነው። የሃሳብ ብዝሃነት እና መርህን ያቀፈ ነው።
- መርሐዊነት ማለት ውይይቶችና ክርክሮች እንዲሁም ሐሳቦች ተፈፃሚነታቸው የፓርቲውን ስነ ስርዓት እና የዴሞክራሲ መርሆዎች የተከተለ መሆን አለበት ነው።

# 4.4 ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን አለማዋለድ…

- የበላይ ሆኖ ለሚወጣ ሐሳብ ተገዥ መሆን የዴሞክራሲ ዋነኛ መርህ ነው።
- የልዩነት ሃሳብ ለመስራት መሞከር ኢ-ዴሞክራሲያዊ ልምምድ ነው።
- የፓርቲ ሚስጢርንና የመድረክ ሁኔታን ወደ ውጭ አውጥተው እየሸጡ ጀግና ጀግና የሚጫወቱትን ፓርቲው አይታገስም።
- ከፓርቲው መርሐዊ አንድነትና ተገዥነት ተፃሮ መቆም ፈፅሞ፣ ፈፅሞ አይፈቀድም።


# ክፍል አምስት

# ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን

# ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን

ከችግሮቻችን ልንሻገር የምንችለው ከችግሮቻችን እየራቅን በሂድን ቁጥር ነው።

ችግሮቻችንን የሚበልጥ ውጤት፣ የባከነውን ጊዜ የሚያካክስ ስኬት፣ ተወዳዳሪነትን የሚያረጋግጥ ውጤት ማምጣት ያስፈልጋል።



የገጠመንን ፈተና መሻገር የምንችለው ይበልጥ በመፍጠር እና ይበልጥ በመፍጠን ነው።

ፍጥነትን ለመጨመር እና ፈጠራን ለማጠናከር ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው።

# ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን…

## 5.1 “የብልጽግና አጣዳፊነት” እሳቤ፣

- ብልጽግናን ባረጋገጡ የትኞቹም ሀገራት ውስጥ የአመራር ሚና እጅግ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው፣
- ስለሆነም የብልጽግናን አጣዳፊነት እና አንገብጋቢነት የተገነዘበ አመራር ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
- ፍጥነትን በመጨመር ብልጽግናን የሚያረጋግጥ መንግስት እንዲኖር የአመራሩ አመለካከትና ባህል መለወጥ አለበት፣
- አመራሩ በጊዜ የለም ስሜት መስራት አለበት፣
- “ይደርሳል” የሚል ደካማ የስራ አስተሳሰብ መቀየር አለበት፣
- በየደረጃው ትኩረትን ከርዕዩ ላይ የማይነቅል አመራር ማረጋገጥ ያስፈልጋል፣
- ለተጓዳኝ አጀንዳዎች የሚውል ትኩረት፣ በፍትጊያ የሚጠፋ አቅም እና ትኩረት በሙሉ ብልጽግናን ወደ ማረጋገጥ እንዳይደርስ የሚያደርጉትን መታገል ያስፈልጋል፣

# ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን...

## 5.2 ነገርን ከስሩ፣

- ከ“አሉ” የድህረ እውነት ፖለቲካ መራቅ፣
- ወቅቱ ነገሮችን ከምንም ነገር በላይ በጥልቀት መመልከት እና ከስሩ መመርመር ይጠይቃል፣
- የመረጃ አብዮት የግራጫ ጦርነትን ፈጥሯል። መረጃን የማዛባት፣ አመለካከትን እና አስተሳሰብን የማደናገር እና ውሳኔን የማስቀየር ጦርነት የዘመናችን መገለጫ ነው።
- አመክንዮአዊ አሰሳ - እውነትን ለማግኘት አመክንዮአዊ ፍለጋ አስፈላጊ ነገር ነው።
- ችግሮችን ከምንጩ ማጤን (ROOT CAUSE ANALYSIS) እና የሚሰራጩ መረጃዎችን በጥልቀት መነፅር (CRITICAL THINKING) መመልከት፣

# ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን...

## 5.3 አዳዲሶቹን ወደ ትግበራ ነባሮቹን ወደ ስራ - ገበታ ለትውልድ፣

- ፓርቲያችን የዛሬን እና የነገን ትውልድ አሻራዎችን ማስቀመጥ ላይ ያተኩራል።

## 5.4 በክረምት፣ እራትና መብራት፣

- የአረንጓዴ አሻራ ስኬትን ማስቀጠል፣
- የደን ሽፋናችን ወደ 17% አድጓል።
- የሌማት ትሩፋት ጅምሮችን ማስፋት፣

# ይበልጥ መፍጠር፣ ይበልጥ መፍጠን…

## 5.5 የወል እውነትን የማጽናት ቀጣይ የፖለቲካ አቅጣጫዎች

ገንቢ ዎች መሆን፣ ከአፍራሾች በላይ መጠንከር፣ ከአፍራሾች በላይ መወሰን፣ ከአፍራሾች በላይ መስዋዕትነት መክፈል፣

በምንገነባት ኢትዮጵያ የሁላችንም የወል እውነት ገዥ ሐሳብ እንዲሆን፣ ለምንፈልጋት ሀገር ለመክፈል የተዘጋጀነው የገንቢነት ዋጋ ይወስነዋል።

የመናጆ ፖለቲካ ሳይፈታን፣ ለህዝብ በመቆርቆር ሽፋን በተለወሰው ሀገር በታኝ የጥላቻ ፖለቲካ ሳንሸነፍ፣ አሰላለፋችን ሳይደበላለቅብን፣ በአመለካከት ሳንሰለብ፣ የወል እውነታችን አሸናፊነትን ወደምናረጋግጥበት ረጅም የብልጽግና ጉዞ እስከ መዳረሻው ለመድረስ በትክክለኛ ባቡር ላይ ተሳፍረናል ወይ? የሚለው የአመራሩና የአባሉ ወሳኝ ጥያቄ ነው።

# ቀጣይ የፖለቲካ ስራችን የወል እውነታዎች መሰረት የሆኑትን የፍትህ፣ የነፃነት እና የእኩልነት ፍላጎቶች ምላሽ እንዲያገኙ የሚከተሉትን ቁልፍ የፖለቲካ ስራዎች መስራት

1. የውስጠ ፓርቲ አንድነት ማጎልበት፣

በተልዕኮዎቻችን የጠራ አቋም መያዝ፣ በሚፈጠሩ አጀንዳዎች አለመጠለፍ፣ በመንገዳችን ጸንተን መቆም፣ የወል እውነቶች ገዢ የሚሆኑበት ስርዓት መገንባት፣

2. ከአንፃራዊ ሰላም ወደ ተሟላ ሰላም መሸጋገር፣

የሰላም ንግግሮችን ማበረታታት፣ የተሃድሶ ኮሚሽንን ማጠናከር፣ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ማጠናከር፣ የሽግግር ፍትህ ላይ መስራት፣ ሰላማችንን እያወኩ ለመቀጠል በሚፈልጉ ኃይሎች ላይ አስተማሪ ርምጃ መውሰድ እና ማጽዳት፣

3. ሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳካ መደገፍ፣

እንደ ገዥ ፓርቲ የኮሚሽኑ አላማ እንዲሳካ ተግባሩን የሚመራ ኮሚቴ በማደራጀት መስራት፣

## ቀጣይ የፖለቲካ ስራችን የወል እውነታዎች መሰረት የሆኑትን የፍትህ፣ የነፃነት እና የእኩልነት ፍላጎቶች ምላሽ እንዲያገኙ የሚከተሉትን ቁልፍ የፖለቲካ ስራዎች መስራት…

## 4. የነፃነት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሚዛን መጠበቅ

የነጠላ እውነት ቡድናዊ የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ የሚፈልጉ ኃይሎች በነፃነት ስም የጥላቻ ፖለቲካ በማራመድ የህዝቦችን የወል እውነቶች ለማፈን እየተጠቀሙበት መሆኑን መረዳት፣

ዴሞክራሲ ከተጠያቂነት ጋር እኩል ካልተጓዘ ችግር እንዳለው ማሳየት ይገባል፣

በነፃነት ስም ከነፃነት ማሳጣት ሀገር ወደ ማሳጣት ሊያሸጋግሩን የተነሱትን መታገል፣

ነፃነት ያለኃላፊነት ስርዓት አልበኝነት በመሆኑ የአጠቃቀም መዛነፎችን የህግ የበላይነት በማረጋገጥ መስመር ማስያዝ ያስፈልጋል፣

ሀገር ማስቀጠል የፓርቲም፣ የአመራሩ የዜግነትም ግዴታችን በመሆኑ ሚዛን ያልሳተ ህግ የማስከበር ዘረፈ ብዙ ስራ መስራትና በነፃነት ስም የሀገረ መንግስታችን አደጋ የሚሆኑ ኃይሎች በህግ አግባብ መግራት አለብን።

## ቀጣይ የፖለቲካ ስራችን የወል እውነታዎች መሰረት የሆኑትን የፍትህ፣ የነፃነት እና የእኩልነት ፍላጎቶች ምላሽ እንዲያገኙ የሚከተሉትን ቁልፍ የፖለቲካ ስራዎች መስራት…
## 5. የተማከለ ያኃይል አጠቃቀም ትግበራን ከዳር ማድረስ

1

የወል እውነቶቻችን ገዥ የሆኑበትን ስርዓት ለመገንባት የሀይል አጠቃቀም ስርዓት መያዝ የግድ የሚልበት ወቅት ላይ እንገኛለን።

2

የክልል ልዩ ኃይሎችን በማፍረስ ወጥ የሆነ የኃይል አጠቃቀም ተግባራዊ ማድረግ በምንም ምድራዊ ኃይልም ሆነ ምክንያት ወደ ኋላ የምንመልሰው ተግባር አይደለም።

# ቀጣይ የፖለቲካ ስራችን የወል እውነታዎች መሰረት የሆኑትን የፍትህ፣ የነፃነት እና የእኩልነት ፍላጎቶች ምላሽ እንዲያገኙ የሚከተሉትን ቁልፍ የፖለቲካ ስራዎች መስራት…
# 6. የተደራጁ ወንጀሎችን መከላከል

01. የፀረ ሙስና ትግል ማጠናከር፣

02. ሌብነትን በመታገል የህዝብ ቅቡልነት ማሳደግ፣

03. የፍትህ አካላት ሪፎርም ማጠናከርና ለህግ የበላይነት ደጋፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

# 6. ማጠቃለያ

# ማጠቃለያ ...


- ባለፉት አምስት አመታት የገጠሙን ፈተናዎች ዋነኞቹ የአስተሳሰብ ለውጣችንን (Paradigm shift) ለመቀልበስ የተደረጉ ናቸው።
- የነጠላ ቡድናዊ እውነት ገዥነትን ባለበት ለማቆየት እና የሀገራችንን ብሔር ብሔራሰቦችና ህዝቦች ሁለንተናዊ የወል እውነቶች ገዢ ስርዓታዊ እሳቤ ለማድረግ በሚሰሩ አካላት መካከል የሚካሄድ ትንቅንቅ ነው።

የነጠላ ቡድናዊ እውነታቸውን ገዢ ለማድረግ ከሚፈልጉ ኃይሎች ጋር እያደረግነው ያለነውን ትግል በ2 ከፍለን ማየት እንችላለን።

1. በምርጫ የሕዝብን ድምጽ አግኝቶ ስልጣን መያዝ ሲያቅተው በጥላቻ ፖለቲካ የትም ፍጪው ስልጣኑን አምጪው ብሎ ህዝባችንን ደም አቃብቶ ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚታገል፣
   - እነዚህን በመደመር እሳቤ መታገል፣
2. የአስተሳብ ለውጥ የማምጣት ትግላችን ከጅምሩ በፈተና የተሞላ ነበር፣
   - ባለፉት 5 አመታት የገጠሙን አይነት ግዙፍ ፈተናዎች ባለፉት 50 አመታት ኢትዮጵያ ላይ የነበሩ መንግስታትን አልገጠማቸውም፣

# በቀጣይ ትኩረታችን

## 1. ማስቀጠል



በብዝኃ ኢኮኖሚ ፖሊሲያችን ያስመዘገብነውን ጥቅል ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በዚህ ዓመትም መድገም፣

በፖለቲካዊ የማስቀጠል ተልዕኳችን ሰላምን ዘላቂ የማድረግ ሥራችንን ወደ ተሟላ ሀገራዊ ሰላም በማንኛውም አማራጭ ማረጋገጥ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይሆንም።

# በቀጣይ ትኩረታችን

# 2. ማምረት

ብዝሃ ዘርፍ ምርታማነት ማሳደግ፣

የመድብለ ፓርቲ ስራ ማስፋት፣


የአባላት ምልመላ እና የአመራር ብቃት ማሳደግ፣

በአስተሳሰቡ፣ አሰላለፉና አደረጃጀቱ የተሰናሰለ ፓርቲ መገንባት፣

# በቀጣይ ትኩረታችን
## 3. ማስተዳደር

ኢኮኖሚውን ማስተዳደር - የተመረተን ምርት ደረጃውን ጠብቆ ተጠቃሚ ጋር እንዲደርስ ማድረግ፣ የንግድ ቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር፣ ኢኮኖሚያዊ አሻጥር፣ ኮንትሮባንድ፣ ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር እና የምርት ስወራ መከላከል፣

በፖለቲካ - የነፃነት አስተዳደርና አጠቃቀም ሚዛን መጠበቅ፣ የህግ የበላይነት፣ ሀገራዊ ሰላም፣ ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብት፣ የውስጠ ፓርቲ ምርታማነትን መጠበቅ፣ ስርጎ ገብ ማጽዳት፣ የወል እውነቶች ገዥነት ማረጋገጥ፣ ሀገራዊ ምክክር ማሳካት እና የአጀንዳ የበላይነት ማረጋገጥ፣




በፍጥነትና በፈጠራ ሁለንተናዊ ምርታማነታችን ለማስቀጠል መትጋት፣

ሀገር የትውልድ ቅብብሎሽ ውጤት ነች።

# አመሰግናለሁ!